የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 43
ADDIS ABABA 11th July, 2014


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፪/፪ሺ፮ ዓ.ም

የታላቁ አረንጓዴ ግምብ የፓን-አፍሪካ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ................ገጽ ፯ሺ፬፻፴፪


CONTENTS


PROCLAMATION No. 842/2014

Convention Related to the Creation of the Pan-African Agency of the Great Green Wall Ratification Proclamation ........................................Page 7432


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፪/፪ሺ፮

## የታላቁ አረንጓዴ ግምብ የፓን-አፍሪካ ኤጀንሲ መቋቋምን የሚመለከተውን ኮንቬንሽን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የታላቁ አረንጓዴ ግምብ የፓን-አፍሪካ ኤጀንሲ መቋቋምን የሚመለከተውን ኮንቬንሽን በሳህሎ-ሰሃራ የአፍሪካ አገሮች እ.አ.አ. ጁን ፲፯ ቀን ፪ሺ፲ በእንጃሚና የተፈረመ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ይህንኑ ኮንቬንሽን ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 842/2014

## A PROCLAMATION TO RATIFAY THE CONVENTION RELATED TO THE CREATION OF THE PAN-AFRICAN AGENCY OF THE GREAT GREEN WALL

WHEREAS, the Convention related to the creation of the pan African agency of the great green wall was signed by the sahelo-saharian African states on the 17th day of June, 2010 in N'Djamena;

WHEREAS, the house of peoples' representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Convention at its session held on the 3rd day of June,2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የታላቁ አረንጓዴ ግምብ የፓን-አፍሪካ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፪/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የኮንቬንሽኑ መጽደቅ

፩) በሳህሎ-ሰሃራ የአፍሪካ አገሮች እ.ኤ.አ. ጁን ፲፯ ቀን ፪ሺ፲ በእንጃሚና የተፈረመው የታላቁ አረንጓዴ ግምብ የፓን-አፍሪካ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ ፲፪ የአፍሪካ ህብረት የፍትህ እና የሰብዓዊ መብት ፍርድ ቤትን በተመለከተ የተደነገገው ታቅቦ ተመዝግቧል፡፡

## ፫. የአካባቢና የደን ሚኒስቴር ሥልጣን

የአካባቢና የደን ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ኮንቬንሽኑ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Convention Related to the Creation of the Pan-African Agency of the Great Green Wall Ratification Proclamation No.842/2014".

## 2. Ratification

1) The Convention Related to the Creation of the Pan-African Agency of the Great Green Wall signed by the sahelo-saharian African states in N'Djamena on the 17th day of June, 2010 is hereby ratified.

2) Without prejudice to the provision of sub-artile (1) of this Article reservation is hereby made conserning the Afirican Court of Jestice and Human Rights of the provision of Article 12 of the Convention.

## 3. Power of the Ministry of Environment and Forest

The Ministry of Environment and Forest is hereby empowered to undertake, in collaboration with the appropriate federal, regional and city administration government organs, all actions necessary for the implementation of the Convention.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of Julay, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት